# ለህዝባዊ አመጽ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ሶስት ነገሮች

- አንድነት፣ እቅድ እና ሥነ ምግባር

# The Trifecta of Civil Resistance: Unity, Planning, Discipline

**Hardy Merriman**

Originally published: opendemocracy.net, Novemgber 19, 2010
Translated by Engidu Woldie and reviewed by Abebe Gellaw

# TRANSLATOR'S NOTES

ICNC International Center on Nonviolent Conflict

# ለህዝባዊ አመጽ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ሶስት ነገሮች

# ● አንድነት፣ እቅድ እና ሥነ ምግባር

**በሃርዲ ሜሪማን**[1]

ትርጉም በእንግዱ ወልዴ | አርታኢ አበበ ገላው

ለሃይል አልባ (nonviolent) ትግል መከሸፍም ሆነ ስኬት ወሳኝ የሆኑት ሶስት ነገሮች አንድነት፣ እቅድና ሥነ ምግባር (discipline) ናቸው።

## ሃይል አልባ ህዝባዊ አመጽን ምን ውጤታማ ያደርገዋል?

በፖለቲካ "ስልጣን ይነጠቃል እንጂ አይሰጥም" የሚለውን ብሂል የምንቀበል ከሆነ በታሪክ የሚታወቁ ሃይል አልባ (ሰላማዊ) የትግል እንቅስቃሴዎች ከባላንጣዎቻቸው የበለጠ ሃይል ስላላቸው ውጤታማ ሆነዋል ወደሚል መደምደሚያ ያደርሰናል።

ይህ መደምደሚያም ስልጣን ቁሳዊ ሃብትንና ሃይልን (violence) ከመጠቀም አቅም ይመነጫል ከሚለውና በአብዛኞች ዘንድ ከሚታመነው መላምት ጋር ይጋጫል። መላምቱንም ለጥያቄ የተጋለጠ ያደርገዋል። ይህ መላምት ሙሉ በሙሉ ትክክል ቢሆንኖሮ የሰላማዊ ትግል ንቅናቄዎች በትጥቅና በቁሳዊ ሃይል የበለጠ አቅም ካላችው ተቀናቃኞች ጋር ሲነጻጸሩ ተሸናፊ ይሆኑ ነበር።

አንዳንድ ምሳሌዎች ለመዘርዘር ያህል፥

- እ.አ.አ. በ 1930ዎቹና በ 1940ዎቹ ህንዶች ለእንግሊዝ ቀኝ ገዢዎች መጠነ ሰፊና አጠቃላይ ትብብርን በመንፈግ ነጻነታቸውን አግኝተዋል። የኢኮኖሚ ማእቀብ በማድረግ ፣ትምህርት በማቋረጥ፣ አድማ በመምታት፣ታክስ ባለመክፈል፣ህዝባዊ እንቢተኝነት በማሳየት፣ ከስራ በገዛ ፍቃድ በመልቀቅና አገራቸውን ለአገዛዝ ምቹ ባለማድረግ በስተመጨረሻ እንግሊዞች ጥለው ለመውጣት እንዲገደዱ አድርገዋል።

- በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ በአሜሪካ የዜግነት መብት ትግል ንቅናቄ በመንጎመሪ የተደረገው አውቶብስ ያለመጠቀም አድማ፣ እንዲሁም በናሽቪል ለነጮች ብቻ በተፈቅዱ ምግብ ቤቶች ገብቶ መቅመጥን የመሰሉ ሰላማዊ የሆኑ የትግል ስልቶች የእኩልነት መብትን ለማስከበር አስትዋጽዎ አድርገዋል። ተቋማዊ የሆነው የዘር መድሎ ያለበትን ክፍተት በመጠቀም በናሽቪል የተደረገው ለነጮች ብቻ በተፈቅዱ ምግብ ቤቶች ገብቶ የመቀመጥ አድማ በሃገር አቀፍ ደረጃ ተከታዮችን አፍርቷል።

---

[1] እ.አ.አ ኖቨምበር 19 2010 በኦፐን ዴሞክራሲ (Open Democracy) ላይ ታትሞ የወጣው የዚህ ጽሁፍ ደራሲ ሃርዲ ሜሪማን እ.አ.አ ከ 2005 እስከ 2007 በInternational Center on Nonviolent Conflict (ICNC) (አለማቀፍ ሃይል አልባ ግጭት ማእከል) በሃላፊነት አገልግሏል። በጂን ሻርፕ የተጻፍውንና "Waging Nonviolent Struggle: 20th Century Practice and 21st Century Potential" በግርድፍ ትርጉሙ "ሃይል አልባ ትግልን ማካሄድ፡ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ልምዶችና የ21ኛው ክፍለ ዘመን እምቅ አቅም" እንዲሁም " "A Guide to Effective Nonviolent Struggle" "ውጤታማ የሆኑ የሃይል አልባ ትግል መመሪያዎች" የተባለውን መጽሃፍ በተባባሪነት ጽፏል። ጸሃፊው በአሁኑ ጊዜም የICNC ፕሬዚዳንት በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛል።

- ከ 1965-1970 ጥቂት የሆኑና አነስተኛ የገንዘብ አቅም የነበራቸው የተባበሩ የእርሻ ሰራተኞች በካሊፎርኒያ የወይን እርሻ ባለቤቶች ላይ ስኬታማ የሆነ አድማና ተአቅቦ በማድረጋቸው ተሞክሮአቸው በሃገር አቀፍ ደረጃ ተስፋፍቷል።

- በ1986 በፊሊጲንስ የሙብት አቀንቃኞች ስርዓቱን ከከዱ ወታደሮችጋ በመሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ስዎች በአሜሪካ በሚደገፈው የፈርዲናንድ ማርቆስ ፈላጭ ቆራጭ መንግስት ላይ የአደባባይ ተቃውሞ አድርገዋል። የሰላማዊው ተቃውሞ አማራጭ ያሳጣው ፈርዲናንድ ማርቆስ አገር ጥሎ እንዲሰደድ ተገዷል።

- በ1988 በቺሊ ህዝቡ በፈላጭ ቆራጩ አጉስቶ ፒኖቼ አገዛዝ ላይ የነበረውን ፍራቻ ሰብሮ የተቃውሞ ህዝባዊ ዘመቻና ሰላማዊ ሰልፍ አካሄደ። ይህ በአገዛዙ ላይ የተከፈተው ዘመቻና የተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ለፒኖቼ ይደረግ በነበረው ድጋፍ ላይ ተጽዕኖ በማሳረፉ ለፒኖቼ ቅርብ የሆኑ ወታደራዊ ባለስልጣኖች ጭምር በተለይ ተቃውሞው እየተጠናከረ ሲመጣ ለርሱ ያላቸውን ዕምነት ነፈጉት። ፒኖቼም ከስልጣን ተወገደ።

- ከ1980 እስከ 1989 ፖላንዳውያን የአጠቃላይ ትብብር እንቅስቃሴው አካል የሆነና የሶሊዳሪቲ (የትብብር) የሰራተኛ ማህብር በማቋቋም አገራችውን ከሩሲያ አገዛዝ ነጻ አውጥተዋል።

- በ1989 በቼኮዝሎቫኪያ  የ ቨልቨት አብዮት Velvet Revolution (ለስላሳ፣ ሰላማዊና ደም ያላፋሰሰ በመሆኑ የወጣለት ስያሜ ነው) አገሪቱ ከኮምኒዝም ስርዓት በሰላም እንድትሸጋገር አድርጓል። ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የተደረገ ተቃውሞ በ1991 በምስራቅ ጀርመን፣ ላቲቪያ፣ ሉቲየኒያ እንዲሁም በኢስቶኒያ ሰላማዊ ሽግግር እንዲደረግ አድርጓል።

- በ1980ዎቹ በደቡብ አፍሪካ የተደረገው ህዝባዊ እንቢተኝነትና ከውጪ አገራት የተጣለው  ማዕቀብ በ1990ዎቹ መጀመሪያ በዘር መድሎ ላይ የተመሰረተውን የአፓርታይድ ስርዓት ከሃገሪቱ ለመገርሰስ ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል።

- በተከታዮቹ አስርት አመታት ሰርቦች (2000)፣ ጆርጂያውያን (2003) ዩክሬናውያን (2004) የምርጫ ማጭበርበር እንዳይፈጸም ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞችን አስወግደዋል።

- በ2005 ሌባኖሳውያን ግዙፍ ሰላማዊ ሰልፎችን በማድረግ በሶሪያ ወታደሮች ቁጥጥር ስር የነበረችውን አገራቸው ነጻ አውጥተዋል።

- በ2006 ኔፓላውያን ከፍተኛ ህዝባዊ እንቢተኝነት በማሳየት የሲቪል አስተዳደር መልሶ እንዲቋቋም አስገድደዋል።

- ከ 2007 እስከ 2009 ሃይል የተቀላቀለበት ወታደራዊ አመጽና ወታደራዊ አገዛዝ በሰፈነባት ፓኪስታን ጠበቆች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ስብስቦችና ግለሰቦች ባደረጉት ርብርብ ነጻ የሆነ የፍርድ ተቋም ለመገንባትና አስቸኳይ ግዜ አዋጁን መሻር ችለዋል።

## ህዝብ አልታዘዝ ካለ ገዢዎች ሊገዙ አይችሉም

ከላይ የተጠቀሱት ህዝባዊ እንቅስቃሴዎችና አመጾች ስኬታማ ሊሆኑ የቻሉት ስልጣንን (ሃይልን) የተመለከተ አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ በመመስረታቸው ነው። ይኸውም አብዛኛዎቹ ተቋማት፣ ድርጅቶችና በማህበረሰቡ መሃል ያሉ ግንኙነቶች ውጤታማ ለመሆን የአብዛኛውና የተራው ህዝብ ስምምነት፣ ትብብር እንዲሁም ታዛዥነት ያስፈልጋቸዋል። በመሆኑም ህዝብ

በተደራጀና ስልታዊ በሆነ መንገድ ትብብሩን ከነፈገ የማስገደድ ጉልበት ይኖረዋል። ህዝብ አልታዘዝም ካለ ፕሬዝዳንቶች፣ ከንቲባዎች፣ ዋና ስራ አስፈጻሚዎች እና ሌሎች ባለስልጣናት እንደፈለጋቸውና ከቁጥጥር ውጪ ሆነው መግዛት አይችሉም።

ከላይ የተጠቀሰውን ለመፈጸም ሃይል አልባ የሆኑ እንደ አድማ፣ ተአቅቦ፣ የተቃውሞ ሰልፍ፣ ህዝባዊ እንቢተኝነት፣ እንዲሁም ከአገዛዙ በተቃራኒ የሚቆሙ ተቋማትን መመስረትና ሌሎችንም ልዩ ልዩ ዘዴዎች (tactics) መጠቀም ይቻላል። እነዚህም ዘዴዎች ዝም ብሎ ለሞራላዊ ምክንያታቸው ብቻ ሳይሆን ለተግባራዊ ጥቅማቸው ስንል ነው መጠቀም ያለብን። ህዝባዊ አመጽን ጥቅም ላይ ያዋሉ ወገኖች የተጠቀሙት ስልት በሃገራቸውም ሆነ በሌላው ሃገር ውጤታማ መሆኑን በመገንዘባቸው ካሉት አማራጮች ሁሉ ህዝባዊ አመጽ ውጤታማ እንደሆነ ይገነዘባሉ።

## ክህሎቶችና ነባራዊ ሁኔታዎች

አስደናቂና ውጤታማ የሆኑ የሰላማዊ ንቅናቄ ድሎች እንዳሉ ሁሉ በታሪክና በዓለም ወቅታዊ ሁኔታ እንደታየው ያልተሳኩ ወይም ያልተቋጩ ሰላማዊ ንቅናቄዎችም አሉ። ዓለም የፖላንድንና የቼኮዝሎቫኪያን ሰላማዊ አብዮት ባየበት ዓይኑ በቻይና የቲያናሚን አደባባይ ጭፍጨፋንም ተመልክቷል። ባለፈው ዓስርተ ዓመት በበርማ፣ ዚምባቡዌ፣ ግብጽና ኢራን ሕዝቡ ሰላማዊ የሆነን የትግል ስልት ተግባራዊ አድርጓል። ነገር ግን ትግሉ የሚጠበቀውን ያህል ውጤት አላሳየም። በምስራቅ ቲሞር የራስን ዕድል በራስ ለመወሰን በተደረገው ትግል ሕዝባዊ አመጽ መተኪያ የሌለው ስልት ነበር። የህዝባዊ አመጽ የትግል ስልት በአንዳንድ የዓለማችን ክፍሎች በቅኝ ገዢዎች ላይ ለተነሳው ተቃውሞ የሕዝቡን አመጽ ለማቀጣጠል ከፍተኛ ጠቀሜታ ቢኖረውም በፍልስጤም፣ በምዕራብ ፓፑዋ፣ በምእራብ ሰሃራና በቲቤት የነበሩ ትግሎች መቋጫ ሳያገኙ ቀርተዋል።

### በእነዚህና በሌሎች ሰላማዊ ትግሎች መሀከል ላሉት ልዩነቶች ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?

ለሰላማዊ ንቅናቄዎቹ ስኬትና ውድቀት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ለሚለው በጉዳዩ ላይ ዕውቀቱ ያላቸውና ምክንያታዊ የሆኑ ሰዎች ላይስማሙ ይችላሉ።[2] የእያንዳንዱ ሰላማዊ ትግል ሁኔታ ውስብስብና ከሌላው የተለየ በመሆኑ ለውድቀቱም ሆነ ለስኬቱ አንድ ዓይነት ምክንያት ብቻ ነው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ ነው። ከምሁራን፣ ጋዜጠኞች እንዲሁም ከሌሎች እንደሰማሁት መከራከሪያ ከሆነ የሰላማዊ ትግሎቹ የተከተሉት መንገድም ሆነ ውጤታቸው በአብዛኛው የሚወሰነው ትግሎቹ በተካሄዱባቸው አገራት ባሉ የተለዩ ነባራዊ ሁኔታዎችና መዋቅሮች ጭምር ነው።

ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ሃይል አልባ (ሰላማዊ) ትግል ውጤታማ የሚሆነው ጨቋኙ አገዛዝ በሕዝቡ ላይ የግድያ እርምጃ ለመውሰድ ፍቃደኛ በማይሆንባቸው ማሕበረሰቦች ብቻ ነው የሚል መከራከሪያ የሚያቀርቡ አሉ። ሌሎች ደግሞ ለሰላማዊ ትግሉ ውጤታማነት የኢኮኖሚ መስፈርት ማለትም (የኢኮኖሚው ርዕዮተ ዓለም ሁኔታ፣ የገቢ መጠን፣ የሃብት ክፍፍል፣ መካከለኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መኖር ወዘተ)፣ እንዲሁም የማሕበረሰቡ የትምህርት ደረጃ ወሳኝ ናቸው ይላሉ። እንደገና ሌሎች ደግሞ የሃያላን አገሮችና በአካባቢው አገራት የሚገኙ ጉልበተኞች ለሰላማዊ ትግሉ ስኬትና ውድቀት ከሌሎች ምክንያቶች ይበልጥ ወሳኝ ናቸው ይላሉ። በተጨማሪም በሃገሪቱ የሚገኙ የዘውግ ብዝሃነት፣ የፖለቲካና የባህል ታሪክ፣ የህዝብ ብዛት፣ የመሬት ስፋትና ለሎችም ሁኔታዎች የትግሉን ውጤት ይወስናሉ።

---

[2] በዚህ ጽሁፍ ውስጥ "የተሳኩ" የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴዎች ተብለው የተጥቀሱት የተነሱበትን ዓላማ ያሳኩትን ሲሆን፣ "ያልተሳኩ" ተብለው የተገለጹት ደግሞ የተነሱበትን ዓላማ ያላሳኩትን ነው። ይህ አገላለጽም ጊዜያዊ ሊሆን ይችላል። የተሳኩ እንቅስቃሴዎች የተነሱበትን ዓላማ አሳክተው ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ በዩክሬን የተካሄደው ብርቱካናማ አብዮት) ነገር ግን ንቅናቄው የገጠመው ፈተና አብዮቱ የኋልዮሽ እንዲሄድ አድርጎታል። በዩክሬን ስለተካሄደው ብርቱካናማ አብዮት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እ.ኢ.አ ኖቬምበር 17, 2010 ይተጻፈውን "The struggle after people power wins" by Olena Tregub and Oksana Shulyar on openDemocracy) ይመልከቱ። በሌላ በኩል ደግሞ የተነሱበትን ዓላማ ያላሳኩ እንቅስቃሴዎች (በ 1989 በቻይና የተደረገው የዲሞክራሲ ንቅናቄ) ነገር ግን ትግሉ የተነሳበት ዓላማ እንዲሁም ትግሉ ለዓመታት ቀጣይነት እንዲኖረው ያደረጉበት ሁኔታ አለ። በቻይና ስለተደረገው የዲሞክራሲ ንቅናቄ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እ.ኢ.አ ኖቬምበር 17, 2010 ይተጻፈውን "Repression's Paradox in China" by Lester Kurtz on openDemocracy) ይመልከቱ። ንቅናቄዎችን "የከሸፉ"ና "የተሳኩ" በሚል ልዩነት ከፍሎ ማየት አስፈላጊ ነው። እንዲሁም እነዚህ የንቅናቄ ውጤቶች ("የከሸፉ"ና "የተሳኩ") በራሳቸው የሚፍጥሩት አንድምታ ትኩረት የሚሻ ነው።

ከመዋቅራዊና ነባራዊ ምክንያቶች በተጻራሪው የንቅናቄው ግጭቱን የማካሄድ እና የማስቀጠል ክህሎት ወይንም ደግሞ ምሁራን አቅም (agency) የሚሉት ሌላው ምክንያት ነው። ለምሳሌ ትግሉ የመረጠው ስትራቴጂ፣ ሕብረተሰቡን ለማንቀሳቀስና ተሳታፊ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውለው ቋንቋ፣ ከሌሎችጋ ቅንጅት የሚፈጠርበት ሁኔታ፣ ተጻራሪውን ዓላማ ለማድረግ የተቀየሰው ዘዴ እንዲሁም ህዝባዊ አመጽን ለመቀጠል የሚጠቅሙ ሌሎች በርካታ ውሳኔዎች የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ትግሉን የሚፈታተኑ ሁኔታዎችን ለመከላከል ይጠቅማሉ።

በእኔ እይታ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ሁኔታዎችን የሰላማዊ ትግልን የሚያደርጉ ወይም ለመመርመር የሚሹ ሰዎች ይዘነጓቸዋል ወይም በጣም ዝቅተኛ ትኩረት ይሰጧቸዋል። ይህ ለምን ሆነ የሚለው የዚህ ጽሑፍ ዓላማ አይደለም። አንዱ ሊሆን የሚችለው ምክንያት ግን ሰዎች የሰላማዊ ትግል መሰረት አድርጎ የተነሳበትን መነሻ ሃሳብን አያውቁም ወይም ቢያውቁም ይጠራጠራሉ። ይህም መሰረታዊ ጉዳይ ስልጣን ወይም ሃይል ከጨቋኞች ወደ ህዝባዊ ንቅናቄው መሸጋገር እንደሚችል አለማወቅ ወይም መጠራጥር ነው። ከዚህ ይልቅ ሌላ ተዓምር ትግሉን ለስኬት ያደርሳል ብለው ያስባሉ ወይም ይጠብቃሉ።

ሆኖም ግን ከላይ የተጠቀሱት ዘዴዎችና ክህሎቶች ሳይናቁ መዋቅሮችና ሁኔታዎችም ሰላማዊ ትግል ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖራቸው መገንዘብ ይኖርብናል። የተጠቀሱት ዘዴዎችና ክህሎቶች የሰላማዊ ትግል ንቅናቄ ሊገጥመው የሚችል አደጋን ለመቋቋም፣ ለማስወገድ ወይም አደጋውን ለትግሉ በሚጠቅም መንገድ ለመለወጥ ይጠቅማሉ።

ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ የሚውሉ ዘዴዎችና ክህሎቶች ጠቀሜታ፣ አንዳንዴም ቀዳሚ ሐሳቤ በሌሎች እንደ ንግድና የሚሊተሪ ትምህርት ባሉ መስኮች እንደ ተራ ዕውቀት ሊቆጠሩ ይችላሉ። ሰላማዊ ትግል ከነዚህ መስኮች በምን ይለያል ብሎ መጠየቅ ይቻላል። አንድን የጦር ጄኔራል ወይም የአንድ ኮርፖሬሽን ስራ አስፈጻሚን ለስራቸው ስኬት ስልት (strategy) አስፈላጊ መሆኑ ቢነገራቸው ሊስቁ ይችላሉ።

ውድድር ወይም አፎካካሪ ገጠመኞች ውጤታቸው ቀድሞ  በቁሳዊ እውነታ የሚታወቅ ቢሆን ኖሮ The Art of  War “የጦርነት ጥበብ” የተሰኘው የሰን ዙ መጽሃፍ እንዲህ በጣም ዝነኛ አይሆንም ነበር።

በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ ላይ ወደተነሳውና ለህዝባዊ አመጽ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው ወደሚለው ጥያቄ እንመለስ። ጥያቄውን ለመመለስም መጀመሪያ በታሪክ ውስጥ የተደረጉ ሰላማዊ የትግል እንቅስቃሴዎች የተከተሏቸውን ስትራቴጂካዊ የትግል ስልቶችና መልካም ልምዶች እንመልከት። በሰላማዊ ትግል ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የዘዴዎችና የክህሎቶች ዓይነት የትግሉን ውጤታማነት ይወስናሉ፥ እነዚህን በቀላሉ ለማስቀመጥ ለሰላማዊ ትግል ውጤታማነት አስፈላጊ የሆኑትን ጉዳዮች በሶስት ከፍለን እንያቸው፥ እነሱም አንድነት፣ እቅድና ሥነ ምግባር ናቸው።

## አንድነት፣ እቅድና ሥነ ምግባር

በጨረፍታ ስናየው የእነዚህ ሶስት ነገሮች አስፈላጊነት ቀድሞውኑ ግልጽ ይመስላል። ይሁንና የእነዚህ ጉዳዮች ጥልቀታዊ ግንዛቤና ሁለገብ ተጽእኖ ሳይፈተሽ ሰላማዊ ትግልን ከታክቲካል (ዘዴ) አንጻርና  እና ለትግሉ ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ ጥቃቅን የሆኑት ላይ በማተኮር ብቻ የምንመለከት ከሆነ ከላይ የተጠቀሱት ሶስት አንኳር ጉዳዮችን እንስታለን። ሶስቱም መብራራት ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው።

## አንድነት

አንድነት (unity) ለሰላማዊ ትግል አስፈላጊ ነው። የትግሉ ተሳታፊዎች ብዛትና ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስብጥር ወደ አንድ መምጣት የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴዎች ጥንካሬ እንዲኖራቸው ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። ባጭሩ የተሳታፊው ቁጥር ብዛትና ስብጥር ወሳኝ ጉዳይ ነው። ትግሉ ብዛት ያላቸውን ሰዎች ማቀፉ እንቅስቃሴውን ሕጋዊ፣ ሃይል ያለውና በታክቲክ የታገዘ እንዲሆን ያደርገዋል። ውጤታማ የሆኑ የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴዎች የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ትግሉ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጠንክረው ይሰራሉ። ለምሳሌ ወንዶችን፣ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ ጉልማሶችን፣ አዛውንቶችን፣ የከተማና የገጠር

ነዋሪዎችን፣ አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የሃይማኖት ተቋማት አባላትን፣ ገበሬዎችን፣ ሰራተኞችን፣ የንግዱ ማሕበረሰብ አባላትን፣ ሃብታሞችን፣ መካከለኛ ገቢ ያላቸውን፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙትን የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የፖሊስ አባላትን፣ ወታደሮችን፣ የፍትህ አካላትና ሌሎችንም ወገኖች ተሳታፊ ማድረግ መቻሉ ወሳኝ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ውጤታማ የሆኑ የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴዎች የባላንጣቸውን ደጋፊዎች ወደነሱ ለመሳብ ጥረት ያደርጋሉ። የባላንጣን ደጋፊዎች ታማኝነታቸውን እንዲቀይሩ ማድረግና ትግሉን እንዲደግፉ ማድረግ ውጤታማና ቀጣይነት ያለው ህዝባዊ አመጽ ለማኪያሄድና የራዕይ አንድነትን ለመፍጠር ይረዳል። ለምሳሌ ያህል በደቡብ አፍሪካ በተደረገው የጸረ አፓርታይድ ትግል እየተካሄደ ከነበረው ህዝባዊ አመጽ ጎን ለጎን ለብሄራዊ እርቅ ጥሪ በመደረጉ ቀድሞ የዘር መድልዖውን ሲደግፉ ከነበሩ ነጮች ጭምር ትግሉ ሰፊ የሆነ ድጋፍን አግኝቷል።

## እቅድና ስልት

የሰላማዊ ትግል ተሳታፊዎች የትግሉን አቅጣጫ በተመለከተ ውስብስብ የሆኑ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ይገደዳሉ። ውሳኔውን ለመፈጸምም ስልታዊ (ስትራቴጂካዊ) ዕቅድ መንደፍ እጅግ ወሳኝ ነው። ትግሉ የተነሳበት ምክንያት ምንም አሳማኝ ቢሆን ወይም የባላንጣው ድርጊት ምንም ያህል ኢፍትሃዊ ቢሆን በግብታዊነትና በይድረስ ይድረስ በታቀደ ህዝባዊ አመጽ ጭቆና አይወገድም። ከዚህ ይልቅ ህዝባዊ አመጽ ጥንካሬ የሚያገኘው የአመጹ ዕቅድ በሕዝቡ ዘንድ ሲሰርጽና ተቀባይነት ሲያገኝ ነው። ይህም ዒላማውንና ትኩረቱን እንዳይስት ጭምር ይረዳል። ምን ዓይነት ታክቲኮች ጥቅም ላይ ይዋሉ? በምን ቅደም ተከተል ይፈጸሙ? ሁሉን ሊያንቀሳቅሱና ሊያሳትፉ የሚችሉ በህብረተሰቡ ቅሬታዎችና ፍላጎቶች ላይ የተመሰረቱ ሃሳቦችን ማቅረብ፥ ግለሰቦችን ወይም ቡድንን ዒላማ ያደረገ ታክቲክ መዘርጋት፥ በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚከናወኑ ስራዎችን መለየትና የተለያዩ ንቅናቄዎች ቅንጅት እንዲፈጥሩ የግኑኝነት መስመሮችን መዘርጋት የመሳሰሉት ጉዳዮችን መመልከት የሰላማዊ ትግል በፈጠራ የታገዘ ስትራቴጂ እንዲኖረው የሚረዱ ናቸው። እነዚህን ለመፈጸም ሰላማዊ ትግሉ የሚካሄድበትን አካባቢያዊ ሁኔታ ሁሉን አቀፍ ዳሰሳ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ውጤታማ የሆኑ የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴዎች መደበኛና ኢመደበኛ በሆኑ መንገዶች በታችኛው እርከን የሚገኘውን ህዝብ በማዳመጥና ከነሱም መረጃን በመሰብሰብ የራሳቸውን፣ የባላንጣቸውንና ገለልተኛ የሆኑ ሶስተኛ ወገኖችን ሁኔታ ይተነትናሉ። እነዚህ ስራዎች የዕቅድ አወጣጡ ሂደት አካልና በትግሉ ሂደት ወቅት በሚፈጠሩ ግጭቶች ወቅት ጭምር የሚካሄዱ ናቸው።

## ሥነ ምግባር

በመጨረሻም አንድ ስልት (strategy) ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ለሥነ ምግባር (discipline) ተገዢ ሲኮን ብቻ ነው። በሰላማዊ ትግል ውስጥ የሥነ ምግባር ተገዢነት እንዳይኖር ከሚያደርጉ ነገሮች ዋነኛው አንዳንድ የትግሉ ተሳታፊዎች የሃይል አማራጭን ጥቅም ላይ ማዋል ሲጀምሩ ነው። ስለዚህም ለሰላማዊ ትግል ደንብ ተገዢነት፣ ማለትም የትግሉ ተሳታፊዎች ትግሉን በሰላማዊ መንገድ ብቻ ማከናወን (ከባላንጣ ትንኮሳ በሚፈጸምበት ግዜ እንኳ) እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ እንዲሁም ለሥነ ምግባር ተገዢ የመሆን አስፈላጊነት ተከታታይ በሆነ መልኩ በተሳታፊዎቹ ዘንድ እንዲሰርጽ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የሃይል አማራጭን መጠቀም የትግሉን ፍትሃዊነት ከመቀንሱ ባሻገር የትግሉ ባላንጣ የሆነው ወገን የሃይል እርምጃ መውሰድ እንዲቀጥል ምክንያት መስጠት ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪም የትግሉን ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማከናወን በትግሉ ሂደት ብዛት ያላቸው ደጋፊዎችንና ተከታዮችን ለማፍራት (የባላንጣውን ደጋፊዎች ከጎን ለማሰለፍ ጭምር) ይጠቅማል።

በዚህ ጽሁፍ ላይ የተነሱትን ጉዳዮች በሙሉ ለማብራራት መጽሐፍ ማዘጋጀት ሊያስፈልግ ይችላል። በተጨማሪም የሰላማዊ ትግል ጉዳይ ተከታታይ የሆነ ጥናት የሚያስፈለገው ጉዳይ ነው። በየግዜው የሚከሰት አዲስ ሰላማዊ ትግል ጉዳዩን የበለጠ ለመረዳት የሚጠቅም አዲስ እውቀት ይዞ ብቅ ይላል። የሰላማዊ ትግልን ፖለቲካዊና ማህበረሰባዊ ክስተት በተመለከተ ሳይንሳዊና ስነ-ጥበባዊ ቅርጹን ለመረዳትና ለማሳደግ ብዙ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል።

ከላይ የተነሱት ሶስት ቁምነገሮች (አንድነት፣ እቅድና ሥነ ምግባር) ጊዜ የማይሽራቸውና የሰላማዊ ትግል ተሳታፊዎች እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ዘገባ የሚያቀርቡና ጥናት የሚያካሂዱ ሰዎች የአንድን ሰላማዊ ትግል በተመለከተ አጠቃላይ ማዕቀፉን እንዲረዱና ትግሉ ያለበትን ሁኔታ እንዲገመግሙ ይረዳል። በትግሉ ውስጥ አንድነት ይታያል? ትግሉ በእቅድ ይመራል? ተሳታፊዎቹ ለስነ ምግባር ተግዢ ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይረዳል። ሶስቱን መርሆች የሚከተሉ የሰላማዊ ትግል ተከታዮች ወደ ሰላምና ፍትህ የሰፈነበት ዓለም ለሚደረገው ሽግግር ትልቅ ፈር ይቀዳሉ። የወደፊቷ ዓለማችን እነዚህን መርሆች በሚከተሉ ሰዎች ትቀረጻለች።